የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

Ethiopians' Citizen Democratic Union • Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

www.slttunhzb.net sh1@ttomar.net

ማሳሰቢያ_20111230-1_ቍ1መሰዕራ

ነሐሴ ፡ 30 ፡ ቀን ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

# ልዩ ፡ ማሳሰቢያ ።

## የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድ ፡ ጸድቋል ።

የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፥ ደንቡ ፡ በሚፈቅድለት ፡ አገባብ ፥ መክሮና ፡ ዘክሮ ፡ በወሰነው ፡ መሠረት ፥ ቍ.1 ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነዱን ፡ በጉባኤ ፡ አሻሽሎ ፥ ረቂቅ ፡ ሰነዱን ፡ ለመላ ፡ አባላቱና ፡ ዐባሪዎቹ ፡ አስተያየትና ፡ ትችት ፡ ማቅረቡ ፡ ይታወሳል ። ከቀረቡት ፡ የማሻሻያ ፡ ሐሳቦች ፡ ውስጥ ፡ በቂ ፡ ድጋፍ ፡ ያገኙቱ ፡ ከረቂቅ ፡ መሠረታዊው ፡ ደንብ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕደው ፥ የተሻሻለውን ፡ የመጨረሻ ፡ ረቂቅ ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድ ፡ ነሐሴ ፡ 30 ፡ ቀን ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ በጉባኤ ፡ ማጽደቁን ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክሩ ፡ ያስታውቃል ።

በማሻሻሉ ፡ ሥራ ፡ በትጋት ፡ የተባበሩትን ፡ ኹሉ ፡ ከልብ ፡ እያመሰገነ ፥ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፥ አባላቱና ፡ ደጋፊዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድ ፡ በማጥናትና ፡ በማስጠናት ፥ በያሉበት ፥ ዐላማውንና ፡ ዐቅዱን ፡ እንዲያስተዋውቁና ፡ ሰላማዊ ፡ ትግሉን ፡ አጠናክረው ፡ እንዲቀጥሉ ፡ ጥሪውን ፡ ያስተላልፋል ።

ይህ ፡ የጸደቀው ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድና ፡ ማንኛውም ፡ ተጨማሪ ፡ መረጃ ፡ ከመርበቢያችን ፡ ከ ፦

http://www.slttunhzb.net

ይገኛል ።

የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ።